የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስረኛ ዓመት ቁጥር 31ኛ
ሠመራ ሚያዚያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት
ጠባቂነት የወጣ

10th year No 31
Samara- 11th April, 2006

ማውጫ

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ማቋቋሚያ፣ እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን
የወጣ አዋጅ ቁጥር 31/1998 ዓ.ም --------- ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 31/1998 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ማቋቋሚያ፣ እንደገና ማደራጃና ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የፍ/ቤት ውሳኔዎችን፣ ትዕዛዞችን፣ አስተማማኝ ሁኔታ የማስፈፀም ብቃት ያለው ለህግ ታራሚዎና በጥበቃ ሥር ላሉ ሰዎች የጥበ ቃ፣ የእርማት፣ የተሃድሶ፣ ተግባራትን የሚያከናውን በዚህም አማካኝነት ታራሚዎችን በመገንባት ረገድ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት የሚጥርና ለፌደራሉ፣ ለክልሉ ህገጋተ-መንግስታት፣ ሌሎች ህጎችና አገራችን በተለያዩ ጊዜያት ለተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ስምምነቶች ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያግዝ የማረሚያ ቤቶች ተቋም እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በ 1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47/ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ #የአፋር ብሔራዊ ክልል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 31/1998 ዓ.ም; ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ውስጥ፦

1. **#ማረሚያ ቤቶች;** ማለት በህግ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት የሚላኩ ፍርደኛ ታራሚዎች፣ ክሳቸውን በጥበቃ ስር ሆነው የሚከተሉ የቀጠሮ አስረኞችና ሌሎች ተጠርጣሪዎች እንደሁኔታው የሚታረሙባቸውና የሚጠበቁባቸው ተቋማት ናቸው።
2. **#ታራሚ;** ማለት በህግ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት የተወሰነበትን የእስራት ፍርድ ውሳኔ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ በመፈፀም ላይ የሚገኝ የተፈጥሮ ሰው ነው።
3. **#የማረሚያ ቤቶች ፖሊስ;** ማለት በክልሉ ማረሚያ ቤቶች በጥበቃና በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ሥራ ላይ የተሰማራ አባል ነው።
4. **#ቢሮ ወይም የቢሮ ኃላፊ;** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስተዳደርና ፍትህ ጉዳዮች ቢሮ ወይም የዚሁ ቢሮ ኃላፊ ማለት ነው።

አንቀጽ 3

ስለ መቋቋም

1. የአፋር ብ/ክ/መንግስት ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ #ጽህፈት ቤቱ; እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ጽ/ቤቱ በህግና በሙያው የሚኖረው ነፃነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል።

አንቀጽ 4

መደበኛ አድራሻ

የጽ/ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት ሠመራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና ማረሚያ ቤቶች ይኖሩታል።

አንቀጽ 5

ዓላማ

የጽ/ቤቱ ዋና ዓላማ በህግ ስልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ለእርማት ወይም ለጥበቃ የሚላኩትን የህግ ታራሚዎች፣ የቀጠሮ እስረኞችና ሌሎች ተጠርጣሪዎች ተረክቦ በመጠበቅ በመንከባከብና የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥተው ለዘለቄታው ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲመለሱና ከህብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ማድረግ ነው።

አንቀጽ 6

ስለ ጽህፈት ቤቱ ዓላማ

ጽ/ቤቱ የራሱ የሆነ አርማ ይኖረዋል። ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ መሠረት አድርጎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

አንቀጽ 7

የቢሮ ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

የቢሮ ኃላፊው

1. የጽ/ቤቱን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣
2. የጽ/ቤቱን ኃላፊ ሹመት ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፣
3. የጽ/ቤቱን የመምሪያ ኃላፊዎችና የዞን ማረሚያ ቤቶች ኃላፊዎች ምደባ ያፀድቃል፣
4. የጽ/ቤቱን አመታዊ እቅድ ረቂቅ በጀት ሪፖርትና የሥራ አፈፃፀም ከአስተያየት ጋር ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣
5. የታራሚዎች መብት መከበሩንና በአግባቡ ጥበቃ መደረጉን እንዲሁም ታርመውና አምራች ዜጋ ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል፣
6. በጽ/ቤቱ የሚቀርቡትን የአደረጃጀትና የአቅም ግንባታ መርሃ ግብር ጥናቶች ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣
7. የጽ/ቤቱን የሥራ ብቃትና ውጤታማነት ለማሳደግ ተገቢውን እርምጃ ይወሰዳል፣ የቁጥጥር ስራ ያከናውናል።
8. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲፀድቁ ያደርጋል።6

አንቀጽ 8

ስለ ጽ/ቤቱ አደረጃጀትና አመራር

1. ጽ/ቤቱ በቢሮ ኃላፊው አቅራቢነት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚሾም የበላይ ኃላፊ ይመራል፣ ይተዳደራል፣
2. ጽ/ቤቱ ለስራው የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ በመንግስት የሚያስወስን ሠራተኞች ይኖሩታል።

አንቀጽ 9

የጽ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙትን ማረሚያ ቤቶች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ሰራቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
2. የየደረጃውን ማረሚያ ቤቶች መዋቅሩ መሰረት የሰራተኛ ቅጥር፣ ምደባ፣ የደረጃ እድገት፣ ዲስፒሊንና ዝውውር ውሳኔዎችን ተቀብሎ ያፀድቃል፣ ምልምል የማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላትን ይቀጥራል፣ የስተዳድራል፣

3. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ታራሚዎችን ለሰላማዊ ዜግነት የሚያበቃ የቀለም ትምህርት፣ ሙያ ስልጠና የማህበራዊና የካውንስሊንግ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ለዚሁ የሚያስፈልጉትን የስልጠና ማዕከላት ያቋቁማል፣
4. በፌደራልም ሆነ በክልሉ ፍ/ቤቶች በሚሰጥ ውሳኔ ወይም ተዕዛዝ ወደ ሚያስተዳድራቸው ማረሚያ ቤቶ የሚላኩ ታራሚዎች በሰብዓዊ አኳኋን መያዛቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
5. ፍርደኛ ታራሚዎችና በጥበቃ ስር የሚገኙ ሰዎ ከተላላፊ በሽታዎች መጠበቃቸውንና በእርማትም ሆነ በጥበቃ ላይ እያሉ ሲታመሙ ነፃ ህክምና፣ ምግብና መጠለያ እንዲያገኙ ያደርጋል፣
6. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ማናቸውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታቸዉ በሚፈፅሙት ጥፋት አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው እንዲወሰዱ ያደርጋል፣ የቅጣት ውሳኔዎችን ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይሽራል፣
7. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ታራሚዎች በእርማት ወቅት የሚያሳዩት አወንታዊ የባህሪ ለውጥ ሳቢያ በወንጀለኛ መቅጫ ስ ስርዓት ህግ መሠረት በአመክሮ የመለቀቅ፤ ጥያቄ ለመማረሚያ ቤቶች ሲያቀርቡ በአግባቡ መስተናገዳቸውንና ጉዳያቸውን ያለመዘየት ተጣርቶ ለሚመለከተው ፍ/ቤት መቅረቡን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣ ስልጣን ባለው አካል ሲታዘዝም የምህረት ይቅርታም ሆነ የእስራት ቅናሽ ውሳኔዎችን ያስፈጽማል ፤
8. የክልሉን ማረሚያ ቤቶች በሚመለከት ከሌሎች ክልሎችና ከፌደራል ማረሚያ ቤቶች እስተዳደር ጋር የስራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤
9. የንብረት ባለቤት ይሆናል ውለል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
10. ከስራ ባህሪው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ህጋዊ ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 10

የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

1. የጽ/ቤቱ ኃላፊ በዚህ አዋጅ መሠረት ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊው ሆኖ የጽ/ቤቱ ዋና አስፈፃሚ በመሆን ይሰራል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኃላፊው፡-

ሀ/ የጽ/ቤቱን የሰራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል ይቆጣጠራል

ለ/ የጽ/ ቤቱን የስራ እቅድ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድለትም በስራ ላይ ያውላል

ሐ/ በህግ መሰረት በጽ/ቤቱ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፈታል ያንቀሳቅሳል

መ/ ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው ስራ ፕሮግራም በጀት መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ጽ/ቤቱ ይወክላል

ረ/ አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ረቂቅ ደንቦች አዘጋጅቶ በቢሮው በኩል ልክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል

ሰ/ በጽ/ቤቱ ውስጥ በፖሊስነት ከተቀጠሩት ውጭ የድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በፌደራሉና በክልሉ ሲቩል ሰርቪስ ህጎችና ደንቦች መሰረት ይቀጥራል ያስተዳድራል ያሰናብታል

ሸ/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ታራሚዎችን አያያዝ ፤ ጥበቃና ተሃድሶ ስራዎች በሚመለከት ጥናቶች ያስጠና አስፈላጊነቱን በማገናዘብ በስራ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ቀ/ የየደረጃውን ማረሚያ ቤቶች ሰራተኞችና የህግ ታራሚዎች አስተዳደራዊ ጉዳዩችን አቤቱታ ይቀርባል ያጣራል ውሳኔ ይሰጣል

በ/ ዝርዝሩ በአፈፃፀም መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የማረሚያ ቤት ኃላፊዎችን ምደባ በቢሮው ኃላፊ በሚሠጥ መመሪያ መሠረት ያከናውናል፣፤

ተ/ የክልሉን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ሰራተኞች የስራ ብቃት የሚያሳድግ ሙያዊ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ቸ/ ለስራው መሳካት በአስፈላጊው መጠን ከስልጣኑና ከሓላፊነቱ በከፊል ለጽ/ቤቱ የበታች የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

ኘ/ በቢሮው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

አንቀጽ 11

ስለ ጽ/ቤቱ የአስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጉባኤ/ ከዚህ በኃላ -<<ጉባኤ>> እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የጉባኤው አባላት ጥንቅርና ዝርዝር ኃላፊነትን በተመለከተ ይህን አዋጅ መሰረት አድርጎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

ክፍል ሶስት

ስለ ክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ

አንቀጽ 12

በማረሚያ ቤት ፖሊስነት ለመመልመል የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ማናቸውም የክልሉ ነዋሪ በማረሚያ ቤት ፖሊስነት ሲመለመል የሚከተሉትን መመዘኛዎች አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል።
   ሀ. በማረሚያ ቤት ፖሊስነት ለመገልገል ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ
   ለ/ ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና ለክልሉ ህገጋት-መንግስታት ታማኝ የሆነ፤
   ሐ/ በክልሉ ማረሚያ ቤት ፖሊስነት ተቀጥሮ ለማገልገል የሚያስፈልገውን አካላዊ ብቃት የሚያሟላ
   መ/ በህብረተሰቡ ውስጥ በዲስፕሊን ወይም በስነ-ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ
   ሠ. ከዚህ ቀደም በወንጀል ድርጊት ውስጥ የተሳተፈ ያለመሆኑ የተረጋገጠ
   ረ/ እድሜያቸው ከ 18 ዓመት ያላነሰ
   ሸ/ የክልሉን ቋንቋ የሚችል
   ቀ/ የማረሚያ የጥበቃ ሙያ ስልጠና ያጠናቀቀ
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት የሚደረገው ምልመላ በተቻለ መጠን የፆታን ተዋጽኦ ያካተተ ይሆናል
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተመለመለ ማንኛውም ብሄረሰብ የፖለቲካ ድርጅት አባል እንደሆነ በማረሚያ ፖሊስነት ሲቀጠር የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን መተው ይኖርበታል።

አንቀጽ 13

ቃለ መሃላ

ለማረሚያ ፖሊስ ስራ የተቀጠረ ማንኛውም ምልምል ለፌደራሉ ህገ መንግስትና ለአፋር ክልል ህግ ምንግስት ታማኝ በመሆን የተጣለለበትን ህዝባዊ አደራና ሙያዊ ሃላፊነት ለመወጣት ቃለ መሃላ ይፈፀማል የቃለ መሃላው ዝርዝር በደንብ ይወሰናል፡

አንቀጽ 14

¾ ቅጥር ዘመን

1. ማንኛውም ማረሚያ ቤት ፖሊሲ አባል የቅጥር ውል የሚፀናው ብቁነቱ ተረጋግጦ ስልጠናውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይሆናል።
2. ማንኛውም የክልሉ ማረሚያ ቤት ፖሊሲ አባል የግዴታ አገልግሎት ዘመን ሰባት ዓመት ይሆናል ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል።

አንቀጽ 15

የቅጥር ውል ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች

ማንኛውም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባል የቅጥር ውል ሊቋረጥ የሚችለው በሚከተለው ምክንያቶች ይሆናል፡-

ሀ. በሞት

ለ. አባሉ የሥንብት ጥያቄ ሲያቀርብና በደንቡ መሰረት ተቀባይነት ሲያገኝ፣

ሐ. በህኪሞች ቦርድ በተረጋገጠ ህመም ምክንያት ለሥራው ብቁ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

መ. ዝርዝሩ በደንቡ የሚወሰን ሆኖ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለና ወንጀሉ ለሥራው ብቁ የማያደርገው ሲሆን፣

ሠ. ዝረርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ከሥራ ለመሰባበት የሚያበቃ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣

ረ. በጡረታ ሲገለል፣

አንቀጽ 16

መብቶች

ማንኛውም የማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባል በዚህ አዋጅ መሰረት፡

1. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ደመወዝ፣ የደንብ ልብስ፣ ነፃ ህክምና፣ የመጓጓዣ አገልግሎቶችና ሌሎች ልዩ ልዩ አበሎችን ያገኛል፣
2. በጡረታ ህግና ደንብ መሰረት የመጦር መብት ይኖረዋል።
3. ለሴት የፖሊስ አባላት የሚሰጥ የወሊድና የእርግዝና ፈቃድ ጨምሮ የዓመት እረፍት ፈቃድና ሌሎች ልዩ ልዩ ፈቃዶችን ያገኛል።
4. በሥራው ምክንያት በፍ/ቤት ቢከሰስ ጽ/ቤቱ ጠበቃ ያቆምለታል።

5. ከሥራው ጋር በተያያዘ ሁኔታ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ሙሉ ወይም በከፊል የመስራት ችሎታቸውን በዘላቂነት ያጣ የማረሚያ ፖሊስ አግባብ ባለው የጡረታ ህግ የተሰጠው መብት ይከበርለታል።
6. በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ የበላይ ኃላፊዎችን በአግባቡ ይጠይቃል፣ ስህተቶችን ያርማል፣ በውይይት ችግሮችን ይፈታል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የሥልጣን ተዋረዱን ጠብቆ አቤቱታዎችን የማቅረብና ውሳኔዎች የማግኘት መብት ይኖረዋል።
7. በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈፀም ከሚወጣው ደንብ ውጭ ያሉ መብቶችን በተመለከተ የፌደራሉና የክልሉ ሲቪል ሠርቪስ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላት ዘንድም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ 17

ግዴታዎች

ማንኛውም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፦

1. በፌደራሉና በክልሉ ህገጋት መንግስታት የተረጋገጡትን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ሳይሸራረፉ በማክበር በዚህ አዋጅ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግና ሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎችና ደንቦች መሰረት ስራውን ያከናውናል።
2. የእስራት ቅጣታቸውን ለመፈፀም ወደ ማረሚያ ቤት የሚገቡ ታራሚዎች ብቁ ዜጎች ሆነው እንዲወጡ በማረምና በማነጽ ሥራ ላይ አስፈላጊውን ሁሉ ያከናውናል።
3. የየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል መሆን የለበትም።
4. የማረሚያ ፖሊስ ስራውን ሲያከናውን ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ የማሳየት እና በደረቱ ላይ ማንጠልጠል ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 18

የጡረታ መውጫ እድሜ

ማንኛውም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች አባል በጡረታ የሚገለገልበትን እድሜ ጣሪያ አግባብ ባለው የጡረታ ህግ መሰረት ለመንግስት ሠራተኞች የተሰጠው የጡረታ መውጫ እድሜ ይሆናል።

አንቀጽ 19

ወታደራዊ ማዕረግ ስለመቅረቱ

1. ማንኛውም የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባል ወታደራዊ ማዕረግ አይኖረውም። ሆኖም ይህንኑ የሚተካ የማረሚያ ፖሊስ የሆነ ማዕረግና ልዩ ምልክት ይኖረዋል። በዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም የማረሚያ ቤቶች ፖሊስ አባላት የሥራ ክፍላቸውንና የኃላፊነት ደረጃቸውን የያዘ ልዩ ምልክት (ባጅ) ይኖራቸዋል።

አንቀጽ 20

የአሰራር መርሆች

1. በክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ መዋቅር ውስጥ በየደረጃው ባሉት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ዘንድ የቡድን አሰራር ዋና የተግባር አፈፃፀም አቅጣጫ ይሆናል።
2. የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ መዋቅር በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ሥልጣን በመወሰን ኃፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው።
3. ከሥራ እቅድ አነዳደፍ እስከ አፈፃፀምና ግምገማ ድረስ የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በቡድን በመቀናጀት ይሰራሉ፣ የቡድን አሰራሮችም የጋራና የግል ኃላፊነትን ያስከትላሉ።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ስለ ታራሚዎች አያያዝ</u>

<u>አንቀጽ **21**</u>

<u>የታራሚዎች አያያዝና አስተዳደር መርሆች</u>

1. የታራሚዎች አያያዝና አስተዳደር ሰብዓዊነት የተሞላበት ይሆናል፣ ጭካኔ የተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝና የቅጣት አፈፃፀም የተከለከለ ነው።
2. ታራሚዎችና በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች እንደሁኔታው በፆታ፣ በእድሜ፣ በፍርድ መጠን፣ በወንጀል አይነት፣ በጤናና ፍርድ በማግኘት አለማግኘት ረገድ ተለይተው መያዝ፣ መጠበቅና መታረም አለባቸው።
3. ታራሚዎች በቂ ምግ፣ ንፁ አየር፣ በቂ የፀሀይ ብርሃንና ህክምና በነፃ የማግኘት መብት አላቸው።
4. የታራሚዎችን ጤንነትና ደህንነት የሚጎዱ ምግቦች፣ መሳሪያዎ፣ አደንዛዥ እፆችና የአልኮል መጠጦች ወደ ማረሚያ ቤት እንዳይገቡ የተከለከለ ነው።
5. ታራሚዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ሐኪሞችቻው ከሐይማኖት አባቶቻቸውና ከጠበቆቻቸው ጋር እንዲገናኙ መብት አላቸው።
6. ማንኛውም ታራሚ የእስራት ጊዜውን ሲፈፅም በአመክሮ፣ በይቅርታ፣ በምህረት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ እንዲፈታ ሲወሰን ወዲያውኑ ከማረሚያ ቤት ጥበቃ ነፃ በመሆን ይለቀቃል፣ አደራ በስሙ ያስቀመጠው ንብረትና ገንዘብ ቢኖር ይመለስለታል።
7. ታራሚው በሚፈራበት ጊዜ የታሰረበት ወንጀል አይነት፣ የፍርድ ልክ፣ በእስራት ጊዜው የነበረው ፀባይ፣ የተሰጠውን የትምህርትና የሙያ ስልጠና ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ ይሰጠዋል።
8. ፍርደኛ ታራሚ ከችሎታውና ከሙያው ጋር የሚስማማ ተመጣኝ የሆነና ጤንነቱን የሚጎዳ ሥራ እንደዝንባሌው እንዲሰራ ይደረጋል፣ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ሲሰማራ የገንዘብ ክፍያ ይሰጠዋል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል።
9. ነፍሰጡር የሆነች ታራሚ ተገቢ የመቆያ ክፍል፣ ተጨማሪ የምግብና የጤና እንክብካቤ እንድታገኝ ይደረጋል።
10. ከእናቱ ጋር የማረሚያ ቤት የገባ ወይም ነፍሰ ጡር ሆና ገብታ የተወለደ ህፃን እድሜው 3 ዓመት እስኪሆነው ድረስ ለእንድ ታራሚ በተመደቡለት በጀት መጠን ምግብ እንዲያገኝ ይደረጋል።
11. ህፃኑ ማረሚያ ቤት ከገባ ወይም ከተወለደ 3 ዓመት ከሆነው ቤተዘመድ ወይም የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት ተረክቦ እንዲያሳድገው ይደረጋል።
12. ታራሚዎች በማረሚያ ፖሊስ አባል አጃቢነት ለልዩ ልዩ ማህበራዊ ችግሮቻቸው ማቃለያ ፈቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል።

<u>አንቀጽ **22**</u>

<u>ታራሚን ስለ መቀበል</u>

በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ጽ/ቤቱ ማንኛውም ሰው በማረሚያ ቤት እንዲቆይ መቀበል የለበትም።

አንቀጽ 23

ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ስለመሆኑ

በታራሚዎች መካከል በዕድ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በብሔር ብሔረሰብ አባልነት ወይም በማህበራዊ ምንጭ ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

አንቀጽ 24

ስለ መታሰርና ዝውውር መረጃ የማስተላለፍ መብት

ማንኛውም ታራሚ መታሰሩን ወይም በማንኛውም ምክንያት ከታሰረበት ተቋም ወደ ሌላ ተቋም መዛወሩን ለቤተሰቦቹ ወይም ለሚፈልገው ሰው የመናገር መብት አለው።

አንቀጽ 25

የታራሚ ግዴታ

ለጥበቃ ስራ ሥነ-ስርዓት አከባበር፣ ፅዳት ጤና አጠባበቅ፣ ማህበራዊ ግንኙነትና ስለ ሌሎችም ጉዳዮች በሚወጣ ደንብ የሚገለፅ የሥነ-ስርዓት ግዴታዎችን ማክበር አለበት።

አንቀጽ 26

የወንጀል ድርጊት

ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት በወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 27

ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት

የጽ/ቤቱ ከክልሉ ፍ/ቤቶች፣ የፍትህ አስተዳደር አካላት ሌሎች መ/ቤቶች በተጨማሪ ከፌደራሉ መንግስት ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጋር ቀጥተኛ የሆነ የሥራ ግንኙነት ይኖረዋ፣ መረጃዎችን ይለዋወጣል።

አንቀጽ 28

ስለ በጀት

የጽ/ቤቱ በጀት በክልሉ መንግስት የሚመደብ ሲሆን ሌሎች ምንጮችንም ተጨማሪ ሊጠቀም ይችላል።

አንቀጽ 29

የሂሳብ መዛግብት

1. ጽ/ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የጽ/ቤቱ ሃሳብና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ መዛግብትና ሠነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

አንቀጽ 30

ስለ ተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 15/1994 ዓ.ም አንቀጽ 37 ሥር የሰፈረው ድንጋጌ በዚህ አዋጅ ተሸሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 31

ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልል መስተዳድር ም/ቤት ይህንን ›ª ጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 32

መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 33

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ሚያዚያ 3 ቀን 1998 ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር